
# የኮቪድ-19 ዴልታ ዝርያ
# የእውነታ መግለጫ

## የዴልታ ዝርያ ምድነው?

**በሳርስ ኮቭ-2 ቫይረስ ላይ ያለን ግንዛቤ በፍጥነት እየተቀየረ ነው።**
**ቫይረሶች በዘረመል ለውጥ አማካኝነት በተከታታይ ለውጥ ውስጥ ያልፋሉ፣ በዚህም አዳዲስ ዝርያዎችን ይፈጥራሉ። አንዳንድ ጊዜ፣ አዲሶቹ ዝርያዎች ከዋነኞቹ ይልቅ የበለጠ አደገኛ ይሆናሉ።**

የዴልታ ዝርያ B.1.617.2 በመባልም የሚታወቅ፣ በመጀመሪያ የተገኘው ባለፈው ዓመት ሕንድ ውስጥ ሲሆን አሁን በዩኤስ ውስጥ ያሉትን 80 % የሚሆኑ የኮቪድ ሕመሞች ይሸፍናል። (1) የዴልታ ዝርያ ከመጀመሪያው ቫይረስ በበለጠ ፍጥነት የሚዛመት ሲሆን፣ በዴልታ ዝርያ የተያዙ ሰዎች ቫይረሱ በምርመራ በደማቸው ውስጥ በሚገኝ ጊዜ 1000 እጥፍ የሚሆን የቫይረስ መጠን በሥርዓታቸው ውስጥ ይገኛል፤ ይኽም ቫይረሱን ወደ ሌላ ሰዎች መተላለፍ ቀላል ያደርገዋል። (2)




## ዴልታ ከፍተኛ ተጽዕኖ የሚያሳድረው ባልተከተቡ ሰዎች ላይ ነው

**99.5%** ከመቶ የ ኮቪድ-19 ሞቶች አሁን የሚከሰቱት ባልተከተቡ ሰዎች ላይ ነው።

**በሽታው ያለባቸው ሰዎች መጠን እየጨመረ ሲሄድ እና ክትባት የሚሰጥበት ፍጥነት ዝቅተኛ ሲሆን፣ ዝግ ያለ የክትባት አሰጣጥ ፍጥነት ያላቸው ግዛቶች ከፍተኛውን፣ በተለይም በዴልታ ዝርያ ኮቪድ-19 የተያዙ ሰዎች ቁጥር ጭማሪ እያዩ ነው ። (3).**

ሆስፒታል የሚያስተኙ የኮቪድ ህመሞች ወጣት በሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ ቀድሞ ከታየው ይልቅ በልጠው መታየታቸውን ሪፖርቶች ያመለክታሉ። (4) ሕጻናትም እንኳን ውደ ጽኑ ሕሙማን ክፍል እየገቡ ነው። (5) አብዛኞቹ ወጣት እና ጤነኛ የሆኑ ሰዎች ከኮቪድ-19 የሚያገግሙ ቢሆንም፣ በቫይረሱ መያዝ በራሱ የሚያመጣው ስጋት አለ። ሆስፒታል እንዲተኙ የተደረጉ በርካታ ወጣትና ጤናማ ሰዎች የረጅም ጊዜ የኮቪድ-19 ምልክቶችን አሳይተዋል እንዲሁም ቫይረሱን ወደ ሌሎች ሰዎች አስተላልፈዋል። በርካታ የማህበረሰብ ጤና ባለሙያዎች እንደሚያምኑት ያልተከተበ ማንኛውም ሰው ይዋል ይደር እንጂ በዴልታ ዝርያ መያዙ አይቀርም።

የዴልታ ዝርያ ምልክቶች ከኮቪድ-19 የመጀመሪያው ስሪት ጋር ተመሳሳይ ምልክቶችን ያሳያሉ። ይሁን እንጂ፣ ሐኪሞች ሰዎች፣ በተለይም ወጣቶች፣ በበለጠ ፍጥነት በሽተኞች ሲሆኑ እየተመለከቱ ነው። የኮቪድ-19 የረጅም ጊዜ ውጤቶችም ግልጽ እየሆኑ ነው። መካከለኛም ቢሆን እንኳ በኮቪድ ከተያዙ 10 ሰዎች አንዱ የረጅም ጊዜ የደረት ሕመም፣ የትንፋሽ ማጠር እና ከፍተኛ ድካም የመሳሰሉ ችግሮች ይገጥሙታል። ከእነዚህ ሰዎች አብዛኛዎቹ በኮቪድ-19 ከመያዛቸው በፊት ወጣት እና ጤነኛ የነበሩ ናቸው። (6)

**RESPECT US. PROTECT US. PAY US.**

# የኮቪድ-19 ዴልታ ዝርያ
# የእውነታ መግለጫ

## ሰብሮገብ ኢንፌክሽኖች

ምንም ክትባት መቶ በመቶ ውጤታማ አይሆንም፣ ስለዚህ ሰብሮ ገብ ኢንፌክሽኖች ሊከሰቱ እንደሚችሉ ይጠበቃል። በዴልታ ዝርያ የሚያዙ የተከተቡ ሰዎች የበሽታው ምልክቶች አይኖሯቸውም ወይም የጉንፋንን የመሰሉ ቀላል ምልክቶች ለምሳሌ ሳል፣ ትኩሳት ወይም ራስ ምታት እንዲሁም ማሽተት አለመቻልን የመሳሰሉ ምክልክቶች ሊኖሯቸው ይችላሉ።

ከጁላይ 26፣ 2021 ጀምሮ፣ ሙሉ ክትባት ከወሰድ 163 ሚሊዮን ሰዎች ውስጥ በሰብሮገብ ኢንፌክሽን ተይዘው በሆስፒታል ለመተኛት እና ለሞት የተዳረጉ ሰዎች ቁጥር 6584 ነው፤ ይኸም ከተከተቡ ሰዎች 0.00004 በመቶ ነው። (8).

## መደምደሚያ

የኮቪድ-19 ክትባት ሙሉ ለሙሉ በሚባል ደረጃ ሁሉንም የኮቪድ-19 ሕመሞች ይከላከላል። (9) ዝቅተኛ ወይም ዝግ እያለ የሚሄድ የክትባት ፍጥነት በሚታይባቸው ማኅበረሰቦች ውስጥ ጠንካራ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት መስጠት እና እንዲሁም ለሁሉም ሰው ክትባት ተደራሽ የሚሆንበትን ሁኔታ ለመፍጠር ድጋፍ ልናደርግ ይገባል።

የክትባት ተደራሽነት በእኩልነት ላይ የተመሰረተ መሆን አለበት፣ ይኸም ለሚያስፈልጋቸው ሁሉ ከክፍያ ጋር የሚሰጥ የእረፍት ፈቃድን ማካተት አለበት። የክትባት ተደራሽነት ደህንነቱ ለተጠበቀ የሥራ አካባቢ አንዱ ገጽታ ብቻ ነው። ቀጣይነት ያለው የኢንፌክሽን ቁጥጥር እና ስጋት ቅነሳ ላይ መስራት፣ ተገቢነት ያለው የግል ደህንነት መጠበቂያ መሳሪያ (PPE) መቅረቡን ማረጋገጥ እና ከክፍያ ጋር የሚሰጥ የእረፍት ፈቃድ፣ የጤና ክብካቤ ተደራሽነት ለሁሉም መሰረታዊ ሰራተኞች እንዲኖር መጎትጎታችንን መቀጠል አለብን።


[1] NYTimes: “The Delta variant makes up an estimated 83 percent of U.S. cases, the C.D.C. director says”
[2] Nature: “How the Delta variant achieves its ultrafast spread”
[3] July 16, 2021,Press Briefing by the White House COVID-19 Response Team and Public Health Officials
[4] NBC News: “Young, unvaccinated people are being hospitalized with Covid-19 as Delta variant spreads, officials warn”
[5] ABC News: “Mississippi health officials warn about Deltadelta ‘surge’ as 7 children in ICU due to COVID-19”
[6] UC Davis Medicine: https://health.ucdavis.edu/coronavirus/covid-19-information/Delta-variant.html
[7] JAMA: “Symptoms and Functional Impairment Assessed 8 Months After Mild COVID-19 Among Health Care Workers”
[8] CDC: https://www.cdc.gov/vaccines/covid-19/health-departments/breakthrough-cases.html
[9] Washington Post: “New study on Delta variant reveals importance of receiving both vaccine shots, highlights challenges posed by mutations”